ድርጅትነት ቆመው፥ ሕዝቡ ሲራብ የተራቡ፥ ሲጠማ የተጠሙ፥ ሲያለቅስ አብረው ያነቡ ጨርሶ አልነበሩም ማለት አይደለም።

አንድ አይነድ አንድ አይፈርድ እንዲሉ ጥረትና ሙከራቸው የተናጠል እየሆነ በጋራ ጠላት ላይ በጋራ ከማትኮር ይልቅ በእርስ በርስ ሽኩቻ ጥረታቸው እየተዳከመ የሕዝቡም የመከራና የስቃይ ዘመን እየተራዘመ መቀጠል የግድ ሆነ። ሕዝቡም የመከራው ቋጥኝ እጅጉን ቢከብደው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ድርጅቶች ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ የሚል ጥሪ አሰማ። ያለማጋነን የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ለዚህ ጥሪ ምላሽ ከሰጡት ሙከራዎች አንዱና ዋነኛው ነው ማለት ይቻላል።

ኢዴኃኅ የተመሠረተውና ዛሬም እየተንቀሳቀሰ የሚገኘው ተቃዋሚ ሁሉ በሕገወጥነትና በወንጀለኛነት ተፈርጆ በሚታሰርበት በሚሰደድበትና በሚገደልበት በኢሕአዴግ አምባገነን ሥርዓት ውስጥ ነው። እዚህ ላይ አንድ ልብ ሊባል የሚገባ ጉዳይ የኢሕአዴግን ሥርዓት አምባገነን ያሰኘው ተግባሩና ባሕርይው እንጂ ተቃዋሚዎች በጥላቻ የለጠፉበት ስያሜ አለመሆኑን ነው።

የኢሕአዴግ ሥርዓት የአንድ ፓርቲ መንግሥትና የመንግሥት መዋቅሮች ሁሉ በኢሕአዴግ ካድሬዎችና ደጋፊዎች የሚመሩ መሆናቸውን ሁሉም አበጥሮ ያውቀዋል።

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሕግ አውጪዎች ተርጓሚዎችም ሆኑ አስፈፃሚዎች በኢሕአዴግ የሚሰየሙ መሆናቸው ያፈጠጠ ያገጠጠ እውነት ነው።

የኢሕአዴግ ሕገ-መንግሥት መሪውን ፓርቲ በሥልጣን ለማሰንበትና ሌላውን ጨርሶ ለማግለል ሆን ተብሎ በስሌት ተሰርቶ የተደነገገ ነው። የምርጫ ቦርዱ በኢሕአዴግ የተሰየመ ሲሆን የምርጫ ሕጉም የረቀቀውና የተዘጋጀው በኢሕአዴግ መሆኑን በፍፁም መካድ አይቻልም።

በየመሥሪያ ቤቱ በኢሕአዴግ የተሰየሙ ሥራ አስፈፃሚዎችም ቢሆኑ የፓርቲውን ፖሊሲ ደግፈውና ተቀብለው በብዙኅኑ ሰራተኛ ላይ የጫኑ የሥርዓቱ የግፍ ጭነት ቀርቃቢዎች ከመሆን አላለፉም። በነፃ መንቀሳቀስ የሚፈልጉ የብዙኃን ድርጅቶች ሳይቀሩ ዛሬ በኢሕአዴግ እየተሳደዱ ከመዳከማቸውም በላይ በኀልውናቸው ላይ ተቀጥላና ተለጣፊ መተካትን ሥርዓቱ የሰርክ ተግባሩ ካደረገው ሰንብቷል።

ገበሬው በመሬት ግብር በማዳበሪያና በምርጥ ዘር ዕዳ ተቀይዶ ነገር ግን አሻፈረኝን የሙጥኝ ብሎ ደግን ቀን እየናፈቀ ሲሆን ነጋዴው በቀረጥ በኪራይ ቤትና በኢሕአዴግ ቀጥተኛ የንግድ ተግባር ተሳታፊነት ከውድድር እንዲወጣና ለኪሳራ እንዲዳረግ የሚሸረብበት ተንኮልና አሻጥር አልቀለለትም። በድምሩ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በኢሕአዴግ እጅና በሱ ቁጥጥር ሥር ነው።

ኢዴኃኅ የኢሕአዴግ ሥርዓት አምባገነን መሆኑን የሚያምነው በተጠቀሱትና በሌሎችም ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማኅበረሰባዊ ሕፀፆች ምክንያት ጭምር ነው። ከእምነትም ባሻገር ኢዴኃኅ በሰላማዊ ትግል አምባገነኑን የኢሕአዴግ ሥርዓት ለማስወገድ በተግባር መንቀሳቀስ ከጀመረ ውሎ አድሯል። ኢዴኃኅ የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ በጥንቃቄ መርምሮና በመሥራች ጉባኤው ወቅት የተሳተፉት ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ ፍላጎትም እምነትም በመሆኑ ጭምር ነው የኢሕአዴግን አምባገነን መንግሥት ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በሰላማዊ ትግል አሸንፎ ለማስወገድ የወሰነው።

የኢትዮጵያን ሕዝብ በማሳተፍ አምባገነኑን ሥርአት በሰላማዊ ትግል ለማስወገድ እንዲቻልም ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ ማካሄድ አማራጭ የማይገኝለት መንገድ መሆኑን ኢዴኃኅ አጥብቆ ያምናል። በነፃና ፍትኅዊ ምርጫ ተሳትፎም የሚጠበቀውን የሕዝብ ሥልጣን ባለቤትነት ማረጋገጥ ይቻላል ብሎ ኢዴኃኅ ራሱን በማዘጋጀት ተግባር ተጠምዶ ይገኛል።

ይሁን እንጂ የምርጫ ቦርዱ ሕጉና አስፈፃሚዎቹ ለኢሕአዴግ በሚመች መንገድ በተዋቀሩበት ሁኔታ ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ አከናውኖ የሕዝብ ውክልናን ያገኘ መንግሥት መመሥረት

ይቻላል የሚል ቅዠት ኢዴኃኅ በፍፁም የለውም:: ስለሆነም ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ እንዲቋቋም ከምስረታው ማግስት ጀምሮ መወትወት ብቻ ሳይሆን ከመንግሥትም ጋር ድርድር ውስጥ ገብቶ ዛሬም በዚሁ አቋሙ እየገፋበት ይገኛል::
የምርጫ ቦርዱን ገለልተኛ የማድረግ የግድነትና ብሎም የኢሕአዴግን ሕገ-መንግሥት መለወጥ አጥብቆ መጠየቅ ግን በምንም መንገድ ምርጫን ባለመፈለግ መተርጎም የለበትም:: ኢዴኃኅ በነፃና ፍትኀዊ ምርጫ ተወዳድሮ ማሸነፍንም ሆነ መሸነፍን በጸጋ ለመቀበል ምንጊዜም ዝግጁ ነው:: ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ በችሮታ ሊሰጡ የማይችሉ መሆናቸውንም ጠንቅቆ ያውቃል:: ለዚህም ነው ለነፃና ፍትኀዊ ምርጫ መሟላት አጥብቆ እየታገለ የሚገኘው::
ዓለም-አቀፍ የነፃና ፍትኀዊ ምርጫን መመዘኛዎች ለመሟላት የመንግሥት ሥልጣን በያዘው ኃይል ላይ ጫና ለማድረግ የሚቻለው ሁሉ ሳይደረግና ሳይረጋገጥ ከወዲሁ ምንም ይሁን ምን በምርጫው እንሳተፋለን ማለት ገዢው ፓርቲ ያለበትን የሁኔታዎች ማሟላት ግዴታን መወጣት የለብህም የማለትን ያህል ሃላፊነት የጎደለው አስተሳሰብ ብቻ ሳይሆን ለኢሕአዴግ አዳማቂ ከመሆን እንደማያልፍ ኢዴኃኅ ደጋግሞ ለማስገንዘብ ጥሯል:: ይህን በማድረግ ሂደት ምላሹ በምርጫው ባለመሳተፍ የእናቴ ቀሚስ ጠለፈኝ ዓይነት ምክንያት መስጠት ሆኖ የተዛባ ትርጓሜ ከተሰጠው ግን ኢዴኃኅ ጉዳዩን ለባለቤቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከማቅረብ ውጭ ሌላ አማራጭ አይኖረውም::
በመጪው ግንቦት ወር የሚደረገው ምርጫ ነፃና ፍትኀዊ እንዲሆን የምርጫ ቦርዱ ሃላፊዎችና በየደረጃው ያሉ ምርጫ አስፈፃሚዎች ገለልተኝነት ወይም ከአንዱ ተወዳዳሪ (ከኢሕአዴግ) ብቸኛ ሙሉ ቁጥጥር ወጥቶ ሁሉን-አቀፍ የመሆን ዓቢይ ጉዳይና የምርጫ ሕጉ በኢዴኃኅና በሌሎች ድርጅቶች የቀረቡ ማሻሻያ ዋና ዋና አሳቦች ተቀባይነት እንዲኖራቸው ማስፈለጉን ኢዴኃኅ ደግሞ ደጋግሞ አሳስቧል አሁንም ያሳስባል:: በኢሕአዴግ የሚቋቋም የምርጫ ቦርድና የሚመረጡ የምርጫ አስፈፃሚዎች ተጠሪነታቸው ለሾማቸው ለኢሕአዴግ ብቻ ነው:: ከዚህ ያለፈ ተግባር ከነዚህ ክፍሎች መጠበቅ ከእባብ እንቁላል እርግብ እንደመሻት ነው የሚቆጠረው:: ይህ የኢዴኃኅ አቋም ስር ነቀል ለውጥን ከመሻት የመነጨ እንጂ በሚቀጥለው ምርጫ ላለመሳተፍ ምክንያት እንደመደርደር መቆጠር የለበትም:: <u>ልዩነቱ ምርጫን በመፈለግና ባለመፈለግ መካከል ሳይሆን የኢህአዴግን ሥርአት አስወግዶ በምትኩ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤት ለሚሆንበት ሥር ነቀል ለውጥ በቁርጠኝነት በመታገልና ሙሉ በሙሉ በኢሕአዴግ ቁጥጥር ሥር በሚገኝ የምርጫ አስፈፃሚ ቦርድ አስፈጻሚነት ያለምንም ጥያቄ ተሳትፈን በለስ ከቀናን ጥቂት የፓርላማ ወንበሮች እያጠራቀምን በጥገናዊ ለውጥ አንድ ቀን ኢሕአዴግን ልናስወግድ እንችል ይሆናል በሚል ሕልም መካከል ነው::</u>

# <u>የዜና አምድ</u>

## <u>የኢዴኃኅ የአውሮፓ ቅርንጫፍ ይበልጥ እየተጠናከረ መሆኑ ተገለጠ።</u>

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት የአውሮፓ ቅርንጫፍ በልዩ ልዩ የአህጉሩ ዋና ዋና ከተሞች የድጋፍ ኮሚቴዎችን እያቋቋመና ለኢትዮጵያዊው ማኅበረሰብ ራሱን ይበልጥ የሚያስተዋውቅባቸው ዝግጅቶችን በማቅረብ ላይ መሆኑን ከአውሮጳ የኢዴኃኅ የሕዝብ ግንኙነትና የማስታወቂያ ቢሮ የተገኘው መረጃ አመለከተ::
ከዚሁ ጋር የደረሰን መረጃ የኢዴኃኅ የአውሮፓ ቅርንጫፍ መሪዎች ጃንዋሪ 30 2005 እ. አ. አ. በአምስተርዳም ከተማ ከሆላንድ የኢዴኃኅ የድጋፍ ኮሚቴ አመራር አባላት ጋር ተገናኝተው ሰፊ ውይይት ያደረጉ መሆኑን የገለፀ ሲሆን በቀጣይ ተግባራትም ላይ እቅዶች ማውጣታቸውን ጨምሮ አስረድቷል:: እስካሁን በሰባት የአውሮፓ አገሮች የድጋፍ ኮሚቴዎች የተቋቋሙ ሲሆን

## የሰሜን አሜሪካ የኢደኃን አመራር አባላት ከአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ሃላፊዎች ጋር ተወያዩ።

ፌብሪዋሪ 7 2005 እ. አ. አ. የሰሜን አሜሪካ የኢዴኃን ጽ/ቤት ሃላፊዎች ከአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የአፍሪቃ ጉዳይ ተጠሪዎች ጋር ኢትዮጵያ ውስጥ በመጭው ግንቦት ወር ሊካሔድ ስለታቀደው አጠቃላይ ምርጫ፥ ከኤርትራ ጋር ስላለው ቀጣይ ውዝግብና በዚሁ ጉዳይ ላይ በአቶ መለስ ዜናዊ ስለቀረበው ባለ አምስት ነጥብ የሰላም ሃሳብ ተብዬ ፥ ስለ አካባቢው ፀጥታና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ውይይት ማድረጋቸው ተገለፀ።

በዚህ ውይይት የኢዴኃን ሃላፊዎች በተለይ መጪው ምርጫ ፍትሓዊና ነፃ ስለሚሆንበት በዚህም ጉዳይ የአሜሪካ መንግሥት ተፅእኖ ስለሚታከልበት ሁኔታ በጥልቀት የተወያዩ ሲሆን የኢትዮጵያን ዳር ድንበር መከበር አስመልክቶም የኅብረቱን አቋም በተለይም የአቶ መለስ ዜናዊን አዲስ የሰላም ሃሳብ አጥብቀው እንደሚቃወሙና ለአካባቢው ዘላቂ ሰላም መፈጠርና ለኢትዮጵያ ሉአላዊነት መጠበቅ ሲባል ቀጣይ ውይይቶች ስለሚመቻቹበትና ስለሚደረጉበት ሁኔታ ከተጠሪዎቹ ጋር ተወያይተዋል። ይኸው ከአመራር አባላቱ ጋር የሚደረገው ውይይት የሚቀጥል መሆኑንም ለማወቅ ተችሏል።

## ሰብሳቢዎቹ አድማጭ ተሰብሳቢዎቹ ተናጋሪ የሆኑበት ስብሰባ በወሎ ባህል አምባ አዳራሽ ተካሄደ።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ወደ ወሎ በማምራት በውስጣችን የሰፈነውን የዝምታ ድባብ እንስበረው መብታችን እንዲከበርና ነፃነታችን እንዳይደፈር በድፍረት መናገር እንጀምር በህዝባዊ ምርጫ ንቁ ተሳታፊ በመሆን የመብታችንና የእድገታችን ተጠቃሚ ለመሆን ለህዝብና ለሀገር ክብር የሚሰሩ ኢትዮጵያውያን ከውስጣችን እናውጣ የሚሉ የመወያያ ርእሶችን በመያዝ የደሴንና የአካባቢውን ህዝብ አወያይቷል።

በውይይቱ ላይ በኅብረቱ ሊቀመንበር በዶክተር መረራ ጉዲና የተመራ ልዑክ ጥር 8 1997 ዓ. ም. በወሎ የባህል አምባ አዳራሽ እንደተገኘ ቁጥሩ ከሁለት ሺህ በላይ የሚገመት ሕዝብ በታላቅ አገራዊ ስሜት ተቀብሎታል ሲል የኅብረቱ ቃል አቀባይ ገልጿል።

ዶክተር መረራ ጉዲና አቶ ደረጀ ከበደና አቶ ሣህሌ ሰይፉ በየተራ የኅብረቱን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ስለወቅታዊ የሃገሪቱ ሁኔታና ስለ1997 ዓ. ም. ምርጫ ማብራሪያ ይስጡ እንጂ ተሰብሳቢው እምብዛም ቅስቀሳ ሳያስፈልገው ኢሕአዴግ የሕዝብ ጠላትና እንደ ኤች አይ ቪ አመንምኖ ገዳይ የሆነ መንግሥት መሆኑን ጠንቅቆ እንደሚያውቅ ለኅብረቱ አመራር አባላት ሲገልፅላቸው ተደምጧል። የኅብረቱ ልዑክም እንዲህ መሰሉን ውስጣዊ ቁጭት የሚያነሳሳ አስተያየት በማግኘቱ ተሰብሳቢው ብሶቱን እንዲገልፅ መድረኩን በሰፊው ተጠቅሞበታል።

በዕለቱ ከሁለት መቶ አስራ አምስት በላይ ማስታወሻዎች ወደ መድረኩ ተልከው ተገቢ መልስ እንዲሰጥበት የተደረገ ሲሆን ዶክተር መረራ ኢሕአዴግ በደሞክራሲያዊ ምርጫ ተሸንፎ ስልጣን ለቀቀ ማለት ለኤች አይ ቪ ኤድስ መድሃኒት ተገኘ ማለት ነው ካላችሁ የወያኔ ኢሕአዴግ መድሃኒት እናንተ ስለሆናችሁ በምርጫ ድምፅ የመንፈግ መርፌ ወግታችሁ ልትገላገሉት ይገባል ማለታቸውና የደሴና አካባቢው ሕዝብ በውይይቱ ዕለት የኢሕአዴግ ሹማምንት ያደረጉለትን ዛቻ የተቀላቀለበት የቀበሌ ስብሰባ ጥሪ ትቶ በኅብረቱ ስብሰባ መገኘቱ የሚደነቅና ወዳጅና ጠላቱን የለየበት ምእራፍ ላይ መድረሱን አረጋግጦልናል። ስለሆነም እኛም ከእናንተ እናንተም ከእኛ ጋር ሆነን እጅ ለእጅ ተያይዘን የጋራ ጠላታችንን በምርጫ እናሸንፍና ለሕዝብ የሚበጅ መንግሥት እንመሥርት ሲሉ ጥሪያቸውን ማስተላለፋቸው ተዘግቧል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የደረሰን ዜና እንደሚያመለክተው ምርጫን በተመለከተ ኢዴኃን ከመንግሥት ጋር ባደረገው

ድርድር ከቀረቡት የማሻሻያ ነጥቦች ውስጥ እጅግ ጥቂቱ ብቻ ተቀባይነት አግኝተው ተግባራዊ እየሆኑ እንደሆነ ሲገለፅ በዚህ ረገድ መገናኛ ብዙሃንን መጠቀም በመጀመሩ ኅብረቱ ዓላማውን ለኢትዮጵያ ሕዝብ በአማርኛ፥ በኦሮምኛና በትግርኛ ቋንቋዎች በማሰራጨት ላይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ኅብረቱን በመወከል በምርጫ የሚሳተፉ ተወዳዳሪዎችን አገር-አቀፍ በሆነ መልኩ በኅብረቱ የአባላት ምልመላ፥ ሥልጠናና አሰማሪ ኮሚሽን አማካይነት ለማሰማራትም ሰፊ እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑ ሲታወቅ ኢዴኃኅ በነዚህ ጥቃቅን ለውጦች ሳይረካ ዋናውንና መሰረታዊውን የምርጫ ቦርድን ሕጉንና የነዚህንና የሌሎችንም ፀረ-ዴሞክራሲያዊና ፀረ-አገር ድንጋጌዎች ምንጭ የሆነውን የሕገ መንግሥቱን መለወጥ ጉዳይ እንደሚገፋበት ከአመራር አካላት የተገኙ ምንጮችን ጠቅሶ የኅብረቱ ቃል አቀባይ ገልጿል፡፡

## የኢዴኃኅ አመራር በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ስብሰባ አካሄደ።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ታሕሣሥ 21 ቀን 1997 ዓ/ም ( ጃንዋሪ 29፣ 2004 ) መደበኛ ስብሰባውን ማድረጉ ተገለጸ፡፡ በዚህ ከአራት ሰዓት በላይ የፈጀ የስልክ ጉባዔ የኅብረቱ እንቅስቃሴ ዘገባ ቀርቦ ግምገማ በማድረግ ስለ ኅብረቱ የወደፊት አቅጣጫና የሥራ ትልም ውይይት ተደርጓል፡፡ በተለይም በመጭው ግንቦት 1997 ዓ/ም በሚደረገው አጠቃላይ ምርጫ ኅብረቱ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ በተመለከተ ጉዳዩ በሰፊው የተመረመረ ሲሆን በኅብረቱ ውሳኔና አቋም መሠረት ምርጫው ነፃና ፍትሓዊ እንዲሆን ለመንግሥት ያቀረባቸው የማሻሻያ ነጥቦች ተቀባይነት እንዲያገኙ በድርድሩ እንዲገፋ በመንግሥት ላይ ጫና ለማሳደር በሚቻለው ሁሉ ትግሉ እንዲቀጥልና የምርጫው ሒደት ዝግጅት በስፋት እንዲጎለብት በሙሉ ድምጽ መወሰኑን ከአመራሩ ቃል አቀባይ ቢሮ የተገኘው ዜና አብራርቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አመራሩ የኅብረቱን አገር-አቀፍ ትግል የሚያጠናክሩ ስልቶችና መንገዶችም ላይ በዝርዝር መነጋገሩና ውሳኔዎች ላይ መደረሱ ታውቋል፡፡

በዚህ የስልክ ጉባዔ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት ተወካይ ዶ/ር አሥራቴ ኃይሌ የተካፈሉ ሲሆን በኅብረቱ አስቸኳይ ጉባዔ በተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብና በተደነገገው መሠረት የኅብረቱ ምክትል ሊቀ-መንበር ሆነው መመረጣቸውን የደረሰን ዜና ጨምሮ ገልጿል፡፡

ኅብረቱ በአሁኑ ወቅት በጉባዔ የተመረጡ ዘጠኝ አባላትን ያቀፈ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ከያንዳንዱ አባል ድርጅት ሁለት ተወካዮች የሚገኙበት (በአስራ አራቱ የወቅቱ አባል ድርጅቶች ቁጥር መሰረት) ሃያ ስምንት አባላትን ያቀፈ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እንዳሉት ይታወቃል፡፡

# ከኢዴኃኅ ማኅደር

*በዚህ አምድ ላይ ቀደም ሲል ኅብረቱ የወሰዳቸውን አቋሞችና መተክላዊ እምነቶቹን ከማህደሮቹ እየፈተሸን እንዳሉ እናቀርባለን፡፡*
*ነገርን ከስሩ እንዲሉ ለዛሬም ከመስራች ጉባዔው ሰነዶች እነሆ።*

*ሐምሌ 23 ቀን 1995 ዓ/ም*

*ከሐምሌ 19 ቀን ጀምሮ በሚካሄደው ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ቀጣይ ስብሰባ ዛሬ ሐምሌ 23 ቀን 1995 ዓ/ም በውይይት ርእሰ-ነጥብነት የቀረበው --የኅብረት ጥረቶች፣ ጥንካሬዎች፣ ችግሮችና ድክመቶች ግምገማ-- ሲሆን ካለፉ ልምዶች ትምሕርት ለመቅሰምና ለወደፊት ያለፉትን ስህተቶች የማይደግም ጠንካራ ኅብረት ለመፍጠር (ለመመሥረት) ይረዳ ዘንድ ያለፉትን ጥረቶች አሉታዊና አዎንታዊ ገጽታዎች ቀጥተኛነትና ፍጹም ግልጽነት በተሞላበት መንፈስ በጥሞና በመመርመር ሰፋና ጠለቅ ያለ ውይይት ተደርጎ የሚከተሉት የጋራ ግንዛቤዎች ላይ ተደርሷል።*

1. አገራችንን ከወደቀችበት የአምባገነን አገዛዝ ለማላቀቅ የሚታገለው የተቃዋሚ ጎራ የትግል ክንዱን ለማስተባበር እንዲችል በአለፉት አሥራ ሁለት (12) ዓመታት በርካታ የኅብረት ጥረቶችና ሙከራዎች እንደተደረጉ፤
2. በርካታና ተደጋጋሚ ሙከራዎች ቢደረጉም በታሰበውና በተፈለገው መልክ ትግሉን በቀጣይነት የሚመራ ጠንካራ ኅብረት እውን መሆን እንዳልተቻለ፤
3. የተደረጉት የኅብረት ጥረቶች በርካታ አዎንታዊ ውቴቶች እንዳስመዘገቡ ሁሉ ባኒያው ብዙ ድክመቶች እንደነበሩአቸው ጉባዔው ተገንዝቧል።

(<u>ማሳሰቢያ</u> ፦ ቀደም ሲል የነበሩ የጋራ ሥራ ጥረቶችን፣ ኅብረትም ይሁኑ ቅንጅት፣ ግንባርም ይሁኑ የትብብር መድረኮች በጠቀላላው ለአቀራረብ እንዲመችና አንድ ወጥ ንባብ እንዲሆን በሚል በሙሉ --ኅብረት-- እየተባሉ ይጠቀሳሉ።)

## <u>ሀ. አዎንታዊ ገጽታዎች፤</u>

1. አገራችንን ከጎጠኛ አምባገነን አገዛዝ ለማላቀቅ በሚደረገው ትግል የተቃዋሚዎችን በጋራ የመቆም አስፈላጊነት ታምኖበት በጋራ ለመታገል ላለፉት 12 ዓመታት የተደረጉት የጋራ ሥራ ጥረቶች ሁሉ የመኖራቸው መንፈስ በራሱ እንደጠንካራ ጎን መቆጠር እንዳለበት፤
2. በርዕዮት ተለያይተው በጠላትነት ይተያዩ የነበሩ ድርጅቶች በጋራ መሥራት መቻላቸው የአገርና የወገን ከባድና ክቡር ዓላማ ዓላማው ለሆነ ሁሉ በልዩነት በጋራ መሥራት እንደሚቻል በጥሩ ምሳሌነት የሚወሰድ አዎንታዊ አስተዋጽዖ እንደሆነ፤
3. የጋራ ትግል ማካሄድ የተሻለ ውጤትን እንደሚያስገኝ በተናጠል ለቆሙ ድርጅቶች መቀራረብ ምክንያት በመሆን በተለይ በሥልጣን ላይ ያለው አካል እንደወጠነው ሕዝቡ እንዳይበተንና እንዲሰባሰብ ማስቻሉና ለማራጭ ሆኖ መገኘቱ፤
4. ለኢትዮጵያ ሕዝብ በቀውጢ ቀን ለችግሩ ደራሽና የጋራ ጩኸቱን የሚያሰማለት፣ የአገዛዙን ብልሹና ፀረ-አንድነት ፖሊሲዎች ለመቋቋም የሚችል የተባበረ ኃይል እንዳለና በጋራ መቆም መቻሉን ማስመስከራቸው፤
5. በዓለም አቀፍ ደረጃ የአገሪቱን ችግሮችና የሚደርሱባትን በደሎች በጋራ ለማሳየት መሞከራቸው፣ በኢትዮጵያዊነት የጋራ ድምጽ በማሰማት ለአገር አንድነትና ለሕዝብ የጋራ መብቶች በመቆም አለኝታነታቸውን ማሳየት መቻላቸው፤ እንደጠንካራ ጎኖች ታይተዋል።

## <u>ለ . ድክመቶች፤</u>

1. ቀደም ሲል የተደረጉ የኅብረት ጥረቶች የአመሠራረት ችግር ነበረባቸው። እነኝህ ኅብረቶች በአብዛኛው ለአንድ የተወሰነ ቀውስ አስቸኳይ ምላሽ ለመስጠት ሲባል በቂ ዝግጅትና ጥናት ሳይደረግባቸው በጥድፊያ የተጠሩ በመሆናቸው አንዳንድ መወገድ የሚችሉ ስህተቶችና እክሎች እንደገጠሙትና የጋራ ሥራው ላይ እንዳጠሉበት፤
2. ፈቃደኛ ሆነው መካተት የሚችሉ ድርጅቶችን ሁሉ ማቀፍ አለመቻሉ፤
3. ውይይት የሚደረግባቸው ርእሰ-ጉዳዮች ላይ በቂ ቅድመ ዝግጅት አለመደረጉ፣ በመሆኑም በጋራ በሚሠሩ ጉዳዮች ላይና ዓላማው ላይ ጭምር የጠራ ግንዛቤ መጨበጥ አለመቻል፤
4. በሁሉም የኅብረት ተሳታፊ ድርጅቶች ዘንድ ከእያንዳንዱ አባል ድርጅት ምን ዓይነት ድርጅታዊ መስዋእትነትን እንደሚጠይቅ የጠራ ግንዛቤ አለመኖርና በግልጽ አለማስቀመጥ ፤

23. አባል ድርጅቶች ለኅብረቱ ሥራ የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽዖ አለማድረግ፥ ማድረግ አለመቻል ፤
24. ያለቦታውና ባላስፈለገ መልኩ የአንዳንድ ሲቪክ ድርጅቶች በፖለቲካ ድርጅቶች አሠራርና ግንኙነት ጣልቃ መግባት ለድርጅቶች መከፋፈልና ለትግሉ መዳከም አስተዋጽዖ ማድረጉ፤ በኅብረቱ አባላት መካከል ስህተት ሲኖር ለመተራረም በቂ ጥረት አለማድረግና የግል ጠብን ድርጅታዊ ለማድረግ መሞከር ናቸው።

-----------------------------------

***ብሔራዊ ክብርና ሉአላዊነት የሚረጋገጡት በሕዝብ አንድነት ብቻ ነው!!!***

***የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅምና አገራዊ አንድነት በሕዝብ የተባበረ ትግል እውን ይሆናሉ!!!***